# የፌደራል መንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ መመሪያ ቁጥር 814/2013

የገንዘብ ሚኒስቴር

ነሐሴ/2013

# የፌደራል ኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭመመሪያ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1.አወጪው ባለስልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 31 እና በኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ የፌደራልአስፈፃሚአካላትንሥልጣንናተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 16/1/ረ መሰረት ይህን መመሪያ አወጥቷል፡፡

### 2.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የፌደራል ኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ መመሪያ ቁጥር 814/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

### 3.ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ የፌዴራላዊ መንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭበኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጸምበትን ሥርዓት ለመወሰን ነው፡፡

### 4.ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በዚህ መመሪያው ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎችበፌደራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር /፪ሺ፩፣ እንዲሁምበግዥ አፈጻጸምመመሪያ እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ የተሰጣቸዉን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ መመሪያወስጥ፡-

ሀ/ "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር /፪ሺ፩ ነው፡፡

ለ/ <<የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት>> ማለት የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም**ዕቃዎች**፣ አገልግሎቶች እና **የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ የሚፈጸምበት፣ ወይም የመንግስት ንብረት በሽያጭ የሚወገድበት ሥርዓት**ነው፤

ሐ/ <<ዓመታዊ የግዥ እቅድ>> ማለት የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም የዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች እና አገልግሎቶችግዥ መቼ እና እንዴትእንደሚፈጽሙ የሚገልጽ ሰነድ ነው፡፡

መ/ <<ተጫራች>> ማለት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን ተከትሎ በግዥው ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት ለመሳተፍ የተጋበዘ ወይም ያመለከተ ወይም የሙጨረቻ ሀሳብ ያቀረበ የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

ሠ/ <<አቅራቢ>> ማለት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን ተከትሎ ለመንግስት መ/ቤት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

ረ/ <<የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር>> ማለት ጥፋት በሚፈጸሙቸው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዥ ወይም ሽያጭእንዳይሳተፉ የታገዱ ተጫራቾችን ወይም አቅራቢዎችን ዝርዝር የያዘ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ እና እንደአስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ያለ መረጃ ነው፡፡

ሰ/ <<ማስወገድ>> ማለት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በማጠቀም የመንግስትንንብረትለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ማስተላለፍ ነው፡፡

ሸ/<<የጨረታ ማስታወቂያ>> ማለት የመንግስት መ/ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትሎ ግዥ ለሚፈጸም ወይም የመንግስትን ንብረት በሽያጭ ለማስወገድ ለተጫራቾች የሚያስተላልፈው ጥሪ ወይም ግብዣ ነው፡፡

ቀ/ <<የመንግስት መ/ቤት>> ማለት ለመንግስት ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መካራ ትግበራ የተመረጠ የፌደራል መንግስት መ/ቤት ነው፡፡

ሸ/ <<ተቆጣጣሪ አካላት>> ማለት ከመንግስት ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጣቸውና ኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በማጠቀም የቁጥጥር ሥራ የሚያከናወኑ የመንግስት መ/ቤቶችማለት ሲሆን፣ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ፣ የፌደራል ዋና ኦዲተር፣ የፌደራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ወሳኔ ሰጭ ቦርድን እና ተመሳሳይ ሚና ያላቸውን ሌሎች አካላት ይጨምራል፡፡

ቀ/ <<የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች>> ማለት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በማጠቀም የግዥና ንብረት ሽያጭ ተግባራትን ለማከናወን የተፈቀደላቸወና በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን፣ ቡድኖችን፣ ባለሙያዎችንና ኃላፊዎችን፣ እንዲሁም አቅራቢዎችንና የፋይናንስ ተቋማትንያካትታል፡፡

## 5.የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱመካራ ትግበራ በተመረጡ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ወደፊት ሊካተቱ በሚችሉ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ግዥ እና ንብረት ሽያጭ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ የግዥና ንብረት ሽያጭ አሰራሮች በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በአፈጻጸም መመሪያዎቹ ማነረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ እና በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም፣ እንዲሁም የመንግስት ንብረትአስተዳደር መመሪያዎች ድንጋጌ መካከል ልዩነት ቢኖር በዚህ መመሪያ የተመለከተው ይፀናል፡፡

## 6. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ የግንኙነት ዘዴ

1) ከመንግስት ግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ በኤጀንሲው፣በመንግስት መ/ቤቶች፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች እና አቅራቢዎች፣ በፋይናንስ ተቋማትእና ሌሎች በዚህ መመሪያ በተገለጹት አካላት መካከል፣ እንዲሁም እርስ በእርስ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ በተደገፈ የግንኙነት ዘዴ መሆን አለበት፡፡
2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም ግንኙነት ማለት የግዥ ዕቅድ ይፋ ማድረግን፣ የጨረታ ማስታወቂያን፣ የጨረታ ሰነድ ሽያጭን፣ ማሻሻያና የማብራሪያ አቀራረብን፣ የቅድመጨረታ ስብሰባዎችን፣ የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓቶች፣ የጨረታ ግምገማ ውጤትና አገላለጽ፣ አቤቱታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥን፣ እንዲሁም በወል አስተዳደር ወቅት ያሉና ሌሎች ተያያዥ ግንኙነቶችን ያካትታል፡፡
3) ማንኛውም ሰነድየኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም የቀረበ እስከሆነ ድረስ በሰነዱ ላይ ፊርማ እና ማህተም ማድረግ ሳያስፈልግ ሰነዱ ትክክለኛ እና የህግ አስገዳጅነት እንዳለው ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ተግባር እና ኃላፊነት

## 7.የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የገንዘብ ሚኒስቴር፡-

1) ለሙከራ የተመረጡ የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችየኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ይሰጣል፣
2) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ለመጠቀም እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ ክፍያ ተመን ይወስናል፣
3) የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን በጀትና ሌሎች የፋይናንስ መረጃዎችን ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ጋርማቀናጀት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

## 8.የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፡-

1) የመንግስት ግዥ እና ንብረት ሽያጭ ተግባራት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትለው ሚፈጸሟቸወን ያስተዳደራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣

2) ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በማጠቀም አዲት የሚድረግ፣ የአቤቱታና የጥፋተኝነት ሪፖርት የማጣራት እና ሌሎች በአዋጅና በመሚሪያ የተሰጡ ተግባራትን ያከናወናል፣

3) የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን መተግበሪያዎች የማዋቀር፣ በየጊዜው ወቅታዊ የሚድረግና የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ፍሰትን የሚደራጅት ተግባራትን ያከናወናል፣

4) ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመጣከር ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ትግበራ አግባብነት ካላቸው የመንግስትና የግል ዘርፉ አካላት ጋር ቅንጅታዊ ስራዎችን ያከናወናል፣

5) ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አተገባበር ጋር በተገናኘ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎችን አቅም ለማንባት የሚያስችል ሥልጠና እና ተያያዥ ሥራዎችን ያከናወናል፣

6) ተጠቃሚዎችበኤሌክትሮኒክ ሥርዓት በተጠቃሚ ትእንዲሚዘገቡ ያደርጋል፣ምዝገባወንም ያስተዳድራል፣

7) ዕቃዎችን፣ የግንባታ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን እንደየባህርያቸው በሚለየት ምድብና ዝርዝር ካታሎግ ያዘጋጃል፣

8) ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚገኙ የመረጃ ምንጮችን ማስረት በሚድረግ ወቅታዊና የተጠቃለለየግዥና ንብረት ሽያጭ መረጃዎችን በሚደራጀትና በመተንተንለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፣

**9)** በቂ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ በዚህ መሚሪያ ከተደነገጉ የኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ ሥርዓት ወጭ ግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ለሚፈጸም ከመ/ቤቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን አሳማኝነትና ተገቢነት በመመርመር ይፈቅዳል፣

10) መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን፣ ቅጾችንና ሌሎች ሰነዶችንለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱአጠቃቀም በሚያመች ሚሁኩ ያዘጋጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣

11) እንደአስፈላጊነቱ ለመንግስት መ/ቤቶች ከግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለማከናወን ወል የገባ ሶስተኛ ወገን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን እንዲጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፣

12) ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመጣከር የመንግስት የልማት አጋሮች በኤሌክትሮኒክሥርዓቱ እንዲጠቀሙ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሚጠቀሙበትን አኳኋን ይወስናል፣

13) በዚህ መሚሪያ አንቀጽ 13የተዘረዘሩና ሌሎች ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱአፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ለህዝብ ይፋ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ይፋ ያደርጋል፤

## 9. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ አግባብነት ባለው ህግ ከተሰጠው ዓላማ አተገባበር ጋር በተያያዘ ከዚህ በታች ያሉ ተግባራትን ያከናወናል፡፡

1) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱላይ ሊቃጡ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል የደህንነት ጥበቃ ያደርጋል፣

2) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አጠቃቀም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የደህንነት ተጋላጭነቶችን እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የቅድመ ጥንቃቄዎችን ለመወሰድ ከኤጀንሲው ጋር በትብብር ይሰራል፣

## 10. በኤጀንሲው ወስጥ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን የሚያስተዳድረው የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን የሚያስተዳደረው የሥራ ክፍል፡

1) ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱትግበራ የሚረዱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችንለአቅራቢዎች፣ለመንግስት መ/ቤቶች፣ ለተቆጣጣሪ አካላት፣ ለፋይናንስ ተቋማት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ እና ይፋ የሚያደርግ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፣
2) ሥርዓቱ ጨረታ አየር ላይ የሚወልበትን የመጀመሪያ ቀንና ሰዓት በራሱ የሚያስጀምር ስለመሆኑ፣እንዲሁም የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የሚጨረሻ ቀንና ሰዓትበራሱ የሚዘጋ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
3) ሥርዓቱ የአቅራቢዎችን የወል የአፈጻጸም ደረጃ መረጃ የሚይዝ፣ እንዲሁም መረጃው የመንግስትመ/ቤቶች ለግዥና ንብረት ሽያጭ ጨረታ ግምገማ እንዲጠቀሙ በሚያስችል ሜኩ ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል፣
4) ሥርዓቱ ቁልፍ የግዥ የአፈጻጸም አመላካቾችን መረጃ ለመያዝ እና የተለያዩ ሪፖርቶችን ለመቀመር በሚያስችል ሜኩ የተዘጋጀ መሆኑን ያረጋግጣል፣
5) ሌሎች ለመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ ሥርዓት ትግበራ እና አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ያስተዳድራል፣
6) በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የሚሰጡት ሌሎች ተግባርና ኃላፊነቶችን ይወጣል፣

## 11. የመንግስትመ/ቤትየበላይ ኃላፊተግባርና ኃላፊነት

የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ፡ –

1) የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተከትሎ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት ሽያጭ ተግባራትን ለሚፈጸም የሚያስችል የተሟላ መዋቅር፣የሲስተም አስተዳደርና ሌሎች አስፈላጊ የሰው ሃይል መመደቡን ያረጋግጣል፣
2) የመ/ቤቱ የግዥ እና ንብረት ሽያጭ ተግባራት ይህን መመሪያ እና የአጠቃቀም መመሪያዎችን ማከረት በሚድረግ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተከትሎ እንዲፈጸሙ ይደግፋል ይቆጣጠራል፣

3) በግዥና ንብረት ሽያጭ ሂደት የሚከተፉ የመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አተገባበር ረገድ ከመ/ቤቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያላቸው የውጭ አካላትየሚኖራቸውን ተግባርና ኃፊነት ለመወጣት እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ወስጥ የተመዘገቡ እና በየስራ ድርሻቸው የተመደቡ መሆኑን ያረጋግጣል፣

4) ከመ/ቤቱ ጋር ወል ያላቸው ሶስተኛ ወገኖችየኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱንበማጠቀም የግዥና ንብረት ሽያጭ ተግባራትን እንዲፈጽሙላቸው ወክልና ይሰጣል፣

## 12. የመንግስትመ/ቤቶች የሲስተም አስተዳዳሪተግባርና ኃላፊነት

1) ለመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት አገልግሎት የሚውሉ ተቋማዊ አደረጃጀት እና የተቋሙን ጠቅላላ መረጃ ይመዘግባል፣ወቅታዊ ያደርጋል፣

2) ከግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር የተገናኘ ኃላፊነት ያላቸው የመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ባለሙያዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣

3) በንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሱ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ከግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ የተሰጣቸውን ተግባራት እንዲያከናወኑ የስራ ድርሻ ይመድባል፣

4) በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ስልጣን ወይም ወክልና መሰረት ለመንግስት መ/ቤቱ የግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር የተያያዙ ተግባራት ለማከናወን ወል የገባ ሶስተኛ ወገን ወይም ሌሎች ከወጭ ለሚመጡ አካላት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በማጠቀም ተግባራቸውን ለመወጣት እንዲችሉ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣

**13.** ከመንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ በአዋጁ፣ እንዲሁም በግዥ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎችተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው የሥራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ሠራተኞች ሥራቸውን ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመውማከናወን አለባቸው፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

# <u>በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ስለሚደረግ ምዝገባ</u>

## 14. የመንግስት መ/ቤቶችና የተቆጣጣሪ አካላት ምዝገባ

**1)** የመንግስት መ/ቤቶች፣ እንዲሁም ተቆጣጣሪ አካላት አግባብነት ባለው ህግ እና በዚህ መመሪያመሰረት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ለመወጣት እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

**2)** ኤጀንሲው ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም የመንግስት መ/ቤቶችና የተቆጣጣሪ አካላት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ለማጠቀም እንዲችሉ ተገቢ የምዝገባ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 15.የፋይናንስ ተቋማት ምዝገባ

1) የፋይናንስ ተቋማት ከግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር የተያያዙ የዋስትና፣ የክፍያ እና ተያያዥ ስራዎችን ለማከናወን እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣

2) ኤጀንሲው ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም የፋይናንስ ተቋማቱ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም አግባብነት ካለው የመንግስት አካል እውቅናየተሰጣቸው መሆኑን በማረጋገጥበሥርዓቱ እንዲመዘገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣

## 16. የተጫራቾች ምዝገባ

1) ተጫራቾች በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብ እና እንደ አግባብነቱ በየዓመቱ ምዝገባቸውን ማደስ ይኖርባቸዋል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተመዘገቡ ተጫራቾችመረጃዎቻቸውን በማንኛውም ጊዜ ወቅታዊ ማድረግ ይችላሉ፣

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የግዥ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች በተጨማሪነት በግዥ አግልግሎት ሰጭነት መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣

# <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አጠቃቀም እና ተደራሽነት</u>

## 17. የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አጠቃቀም

1) ማንኛውም በመንግስት ግዥ እና ንብረት ሽያጭ የሚሳተፍ ተጫራች ማናቸውንምከፋይናንስ ተቋማት የሚቀርቡ ክፍያዎች እና ዋስትናዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም የቀረቡ መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

2) ኤጀንሲውበኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ወስጥማንኛውምስህተት ወይም ግድፈት ወይም ስጋት የተከሰተ መኖሩን ሲረዳ ያለቅድሚያ ማስታወቂያ በማንኛውም ጊዜአገልግሎቱን በከፊል ወይም በሙሉ ሊያርም ወይምሊያሻሻል ወይም ሊያቋርጥ ይችላል፤ሆኖም የተወሰደውን እርምጃወዲያውኑ ሥርዓቱን ሲጠቀሙ ለነበሩ አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

3) ኤጀንሲው ላልተጠናቀቁ የግዥና ንብረት ሽያጭ ሂደቶች፣ የመጫረቻ ሰነድ ማስገቢያ ጊዜ በቂ አለመሆን፣ለመረጃ መረብ መቋረጥ፣ ለተጠቃሚዎች መለያዎች መጥፋት፣የድረ-ገጽ መቆራረጥወይምመዘጋት፣አግባብ ባልሆነ አጠቃቀም ወይም በቸልተኝነት ለሚፈጠር ጉዳት፣ ወይም በሌላ በተጠቃሚዎችተግባርለሚፈጠሩ ጉዳቶች ኃላፊነት አይወስድም፡፡

4) የመንግስትመ/ቤቶች ጨረታው አየር ላይ በሚቆይበት ጊዜ በራሳቸው የጥንቃቄ ጉድለት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ለሚፈጠር የጊዜ መቆራረጥ ወይም የመረጃ ተደራሽነት ችግር ተጨማሪ ማካካሻ ጊዜ ማስጠት አለባቸው፡፡

5) የተፈቀደላቸው የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱተጠቃሚዎች የመጫረቻ ሰነዱ ከተከፈተ በኋላ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የሥርዓቱ ተጠቃሚ አስተዳደሪ የተጫራቾችን ሚረጃና ማንነት ማግኘት የለበትም፡፡

6) ለግዥ እና የማውገድ ንብረት ሽያጭ እና ወል አስተዳደር ተግባራት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚገለጹ የተገደቡ ጊዜዎች አቆጣጠር በኤጀንሲው የሚረጃ ማዕከል ሰርቨር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7) ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ተጠቃሚ ተጠቀመውን ኮምፒውተር ትክክለኛውን አሰራር ተከትሎ በመዘጋት ለሌላ ተገልጋይ ጥቅም ላይ እንዳይውል ማድረግ አለበት፡፡

8) ሌሎች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አጠቃቀም ሂደቶች ለዚህ ዓላማ በሚዘጋጀው ዝርዝር የአጠቃቀም ማንዊያ ላይ በሚገለጹት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 18. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሚረጃዎችን ይፋ ስለማድረግ፣

1) የሚከተሉት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሚረጃዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው፣

ሀ/ የመንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያዎች፣ የአሰራር ሰነዶች፣ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ የሚተላለፉ ሰርኩላሮች፣

ለ/ የመንግስትመ/ቤቶች ዓመታዊ የተጠቃለለ የግዥ ዕቅድ እና አፈጻጸም ሪፖርት፣

ሐ/ የግዥና ንብረት ሽያጭ የግልጽ እና የማጣሪያ የግዥ ዘዴዎች የጨረታ ማስታወቂያ፣ እንዲሁም የጨረታ ሰነድ፣

መ/ የተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ ግምገማ ውጤትና የአሸናፊ ተጫራች ማንነት፣

ሠ/ በግዥ ግምገማ እና ንብረት ሽያጭ ውጤቱ ላይ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ ለዚህ ዓላማ በኤጀንሲው በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት የአቤቱታውን ሂደት የሚገልጹ ዋና ዋና ሚረጃዎች፣

ረ/ ወል የገባው አቅራቢ ድርጅት ስም፣ የግዥው ወይም የሽያጩ ዓይነት፣ የወል ጊዜና ዋጋ፣ እንዲሁም የአቅራቢዎች የወል አፈጻጸም የሚያሳዩ ዋና ዋና ሚረጃዎች እና ሌሎች ለዚህ ዓላማ በኤጀንሲው በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የተገለጹ ሚረጃዎች፣

ሰ/ እንደ አስፈላጊነቱ ዝርዝራቸው በኤጀንሲው የሚገለጹ ሌሎች ሚረጃዎች፣

2) የመንግስት መ/ቤቶች በኤሌክትሮኒክሥርዓቱአማካኝነት የሚያሳዩት ወይም የሚያሰራጩት ማንኛውም ሚረጃ ወይም መግለጫ አስተማማኝ፣ ትክክለኛ ወይም የተሟላ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማጠት አለባቸው፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ አተገባበር</u>

## 19.የግዥ እና የንብረት ሽያጭ ዕቅድ

1) የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁና በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ማሰረት ዓመታዊ የግዥና ንብረት ሽያጭዕቅዳቸውንየኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም ማዘጋጀት፣ እንደአስፈላጊነቱ ማከለስና በዚህ መመሪያ ማሰረት ይፋ ማድረግ አለባቸው፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩በተጠቀሰው ዕቅድ ወስጥ ባይካተቱም የመንግስት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ስምምነት ከገቡ አቅራቢዎች ግዥ ለመፈጸም፣ ድንገተኛ፣ አስቸኳይ፣ የዋጋ ማቅረቢያ ወይም ጥቃቅን ግዥዎችን ለዚህ ዓላማ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ የተዘጋጀውን የግዥ ማጠየቂያ በማጠቀም ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ማሰረት የሚዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ እና ንብረት ሽያጭ ዕቅድ ይዘት በኤሌክትሮኒክ ግዥ ዝርዝር የአጠቃቀም መምሪያ ላይ የሚገለጹ ሁኔታዎችን ማካተት አለበት፡፡

## 20.የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዘዴዎች

ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አጠቃቀም ዓላማ የኤሌክትሮኒክ መንግስት ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዘዴዎች እንደሚከተለው ተዋቅረዋል፡፡

### 20.1 የግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ

1) ይህ የግዥ ዘዴ በጨረታው ለመሳተፍ ለሚፈልጉ አቅራቢዎች ሁሉ እኩል ዕድል በሚሰጥ መልኩ የጨረታ ማስታወቂያውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱላይ እና ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ፣ እንዲሁም እንደአግባብነቱ በሌሎች ዘዴዎች ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ የሚፈጸም የግዥ ዘዴ ነው፡፡
2) ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አፈጻጸም በዚህ መመሪያ የተቀመጡ የተለዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ በአዋጁና በአፈጻጸም መመሪያዎች የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

### 20.2 የማጣሪያ ጨረታ የግዥ ዘዴ

**1) የማጣሪያ ጨረታ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም**

የማጣሪያ ጨረታ የግዥ ዘዴ በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾችን ከአንድ ደረጃ በላይ በሆነ ወድድር በማጣራት እና በመጀመሪያው ደረጃ ያለፉ ተጫራቾችን ለቀጣይ ደረጃ ወድድር በመጋበዝ ከተጋበዙ ተጫራቾች መካከል የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ሥርዓት ሲሆን ከዚህ በታች የተመለከቱ አሰራሮችን ተከትሎ ይፈጸማል፣

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች ተጫራቾች በማጣሪያ ደረጃ ወድድሩ በሽርክና ወይም በጋራ እንዲወዳደሩ መፍቀድ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የማጣሪያ ወድድሩን በግል ያለፉ ድርጅቶች በቀጣይ ደረጃ ወድድሮች ላይ በማጣሪያው ካለፉ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር አይፈቀድላቸውም፣

ለ/ በማጣሪያ ደረጃ ወድድሩ በጋራ ወይም በሽርክና የተሳተፉ ድርጅቶች በቀጣይ ደረጃ ወድድር ላይ በግል እንዲሳተፉ አይፈቀድም፡፡

ሐ/ የማጣሪያ ወድድሩ ወጤት እንደታወቀ በወድድሩ ለተሚረጡ እና ላልተሚረጡ ተጫራቾች በእኩል ጊዜ ማለጽ አለበት፡፡

2) የመንግስትመ/ቤቶች ለማጣሪያ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም ዓላማ እንደ አግባብነቱ የሁለት ደረጃ ጨረታ፣ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ወይም የፍላጎት ማጠየቂያ ጨረታየማምረጫ ዘዴዎችን ማጠቀም ይችላሉ፡፡

## 20.3 የወሰን ጨረታ የግዥ ዘዴ

1) የወሰን ጨረታ ግዥ ዘዴ ቁጥራቸው ወሰን የሆኑ ተጫራቾችን በግል የሚልዕክት አድራሻቸው ወይም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ በተሚዘገበው አድራሻቸው በሚለክ ግብዣ ማስረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር የጨረታው አሸናፊ የሚሚረጥበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡

2) የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ አንቀጽ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ላይ የተቀሚጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ የወሰን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተጠቅመው ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

3) የንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖየመንግስት መ/ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ማጠየቂያ የሚፈጸሙ ግዥዎችን በዚህ የግዥ ዘዴ ተጠቅመው ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሂደቱ አዋጁ እና በአፈጻጸም መመሪያዎቹ የተደነገጉ የዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ሥርዓትን ማከተል ይኖርበታል፡፡

## 20.4 የቀጥታግዥ ዘዴ

1) ለኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አፈጻጸም በዚህ መመሪያ የተቀሚጡ የተለዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች በቀጥታ የግዥ ዘዴ የሚፈጸሙ ግዥዎችን በአዋጁና በአፈጻጸም መመሪያዎች የተቀሚጡ ድንጋጌዎችን ተከትለወመተግበር አለባቸው፡፡

2) የመንግስት መ/ቤቶች ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ሳይጠቀሙ መደበኛ ካልሆነ አቅራቢ፣ እንዲሁም በጉዞ ወቅት ለሚገጥሙ ችግሮች የሚፈጽሟቸውን ጥቃቅን ግዥዎች መረጃ ወዲያወኑ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብና ሰነዶቹንም መጫን ይኖርባቸዋል፣

**21.** የመንግስትመ/ቤቶች ለግልጽ ጨረታ፣ ለወሰን ጨረታ እና ለቀጥታ የግዥ ዘዴዎች አፈጻጸም ዓላማ እንደ አግባብነቱ የመጫረቻ ሰነድ ማጠየቂያ፣የማወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ፣ የአማካሪዎች ብቃት ላይ የተማሰረተ ጨረታ እና የዋጋ ማቅረቢያ ማጠየቂያ ዘዴዎችን ማጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

**22.** በጨረታሰነድዝግጅትወቅትበዓመታዊ የግዥ ዕቅዱ ላይ ከተቀማጠው የግዥ ዘዴ ወጭ ለወጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኑ ሲታመንበት ዓመታዊየግዥዕቅዱ በዚሁ ማሰረት መሻሻልና የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## 23. የኤሌክትሮኒክ የግዥና ንብረት ሽያጭ ስልቶች

1) የመንግስትመ/ቤቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳ መሰረት የሚመርጧቸውን የግዥ ዘዴዎች ተከትለው እንደየግዥው ባህርይና ዓይነትተስማሚ የሆነውን የግዥ ስልትማጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡
2) ለንዑስ አንቀጽ ፩ዓላማ የግዥ ስልት ማለት መግዛትን፣ መከራየትን፣ መቅጠርን፣ ወይም በሊዝስምምነት መከራየትን ያካትታል፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት ለመንግስት መ/ቤቶች ለንብረት ሽያጭ አፈጻጸም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ከተቀማጡት ስልቶች ወስጥ መሸጥ የሚለውን በመምረጥ ማጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

# ክፍል ስድስት
# የኤሌክትሮኒክ ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ አፈጻጸም

## 24. የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሂደት፣

### 24.1 የጨረታ ሰነድ ዝግጅትና ሽያጭ

ሀ/የመንግስት መ/ቤቶች ለኤሌክትሮኒክ ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ የጨረታ ሰነድ አዘገጃጀት ዓላማበኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የመረጃ ቋት የሚገኘውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ቅጾች ማጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

ለ/ ተጫራቾች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱንበማጠቀምለጨረታ ሰነድ ሽያጭ የሚጠየቀውን ክፍያሲፈጽሙ ወይም እንደሁኔታው ያለ ክፍያ የጨረታሰነዱበኤሌክትሮኒክሥርዓቱ አማካኝነት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቶች በጨረታ ሰነድ ዝግጅት የወጭ አገር ተጫራቾች ዋጋቸውን የሚያቀርቡበትን የዓለም ዓቀፍ የንግድ ቃልዓይነት በጨረታ ሰነዱ ላይ በቅድሚያ ማመላከት ይኖርባቸዋል፡፡

መ/ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥው ዓለም ዓቀፍ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ የመንግስት መ/ቤቶች የአገር ወስጥ እና የወጭ አገር ተጫራቾችን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማወዳደር ዓላማ የሚገለግል የዓለም ዓቀፍ የንግድ ቃል ዓይነት በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

ሠ/ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) አፈጻጸም መ/ቤቶች ለግምገማ ዓላማ የሚጠቀሙቸው የአገር ወስጥ ወጪዎች መረጃ ጨረታው ይፋ የሆነበት ቀን ወይም ይፋ ከሆነበት ቀን አስቀድሞ ያለ የቅርብ መረጃ መሆን ያለበት ሲሆን ይህም በጨረታ ሰነዱ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

### 24.2 የጨረታ ማስታወቂያ

የመንግስት መ/ቤቶች ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው የጨረታ ማስታወቂያ ጥሪ ሲያስተላልፉ የሚከተሉትን አሰራሮች ማከተል አለባቸው፡፡

ሀ/ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን የኤሌክትሮኒክ ቅጽ በመጠቀምየጨረታ ማስታወቂያ ወይም ግብዣ ማዘጋጀትና በተመሳሳይ ጊዜ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱእና ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የጨረታ ማስታወቂያውን ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) መሰረት በጋዜጣ ላይ የሚወጣው የጨረታ ማስታወቂያ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚያገኙበትን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አድራሻ እና ግዥው የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትሎ የሚከናወን መሆኑን የሚያመለክት መግለጫ ማካተት ይኖርበታል፡፡

ሐ) በጨረታ ማስታወቂያው ይዘት፣ እንዲሁምጨረታው አየር ላይ የሚቆይበትን ጊዜአቆጣጠር በሚመለከት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ እና በጋዜጣ ላይ በሚወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢኖር በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ያለው የበላይነት ይኖረዋል፡፡

መ) ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ የሚወሰነው ከፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ጋርበተያያዘው አባሪ ፫ መሰረት ሲሆን፣ጨረታው አየር ላይ የሚቆይበት ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያው በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ላይ ከመወጣበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ይቆጠራል፡፡

## 24.3 የቅድመ ጨረታ ስብሰባ

ሀ) የቅድመ ጨረታ ስብሰባ የሚድረግ አስፈላጊነቱ ከታመነበት የመንግስትመ/ቤቶች ስብሰባውን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም ማካሄድ አለባቸው፡፡

ለ)የመንግስት መ/ቤቶች ለፊደል ተራ (ሀ) አፈጻጸምየቅድመ ጨረታ ሰብሰባ የሚደረግበትን ቀንና ሰዓት፣ እንዲሁም የሰብሰባ መለያ ቁጥር በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለጽ አለባቸው፡፡

ሐ) የመንግስትመ/ቤቶች የቅድመ ጨረታ ስብሰባውን ሁኔታ እና ሂደት የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ ማያዝና የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ለተሳታፊዎች መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

## 24.4 የጨረታ ማሻሻያ ስለሚድረግ፣

ሀ) የጨረታ ማሻሻያው ከቀነ ገደቡ በፊት ባሉት አምስት ቀናት ወስጥ የወጣ ከሆነ የመንግስትመ/ቤቶች ዕጩ ተወዳዳሪዎች **የመጫረቻ ሰነዳቸውን አሻሽለው ለማዘጋጀት በቂ ጊዜእንዲኖራቸው ለማድረግ** ጨረታው የሚዘጋትን ቀን ቢያንስ ለተጨማሪ አምስት**ቀናት ማራዘም** አለባቸው፡፡

ለ) በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ሽያጭ የጨረታሰነድ ላይየሚደረግ ማንኛውም ማሻሻያበዋናው የጨረታ ሰነድ ላይ መደረግ ያለበት ሲሆን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች በኤሌክትሮኒክ አድራሻቸው እንዲደርስ መደረግና በተጨማሪም በሥርዓቱ አማካኝነት ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

## 24.5 የመጫረቻ ሰነድ ስለማዘጋጀትና ስለማቅረብ፣

1) ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አማካኝነት ለሚከናወን ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ለማተፍ የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ዝግጅትና አቀራረብ በግዥ አዋጁና መመሪያው ላይ የተደነገጉ ሥነ ሥርዓቶችን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡
2) የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖለመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥናንብረት ሽያጭ የሚቀርብ ማንኛውም የመጫረቻ ሰነድ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትሎ ማዘጋጀትና መቅረብአለበት፡፡

## 24.6 ጨረታን ስለመክፈት

የመንግስትመ/ቤቶች ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ግዥ ሲፈጽሙ ንብረት ሲያስወግዱ የሚከተሉትን የጨረታ አከፋፈት ሥነ ሥርዓት መከተል አለባቸው፡፡

ሀ) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚደረግ ማንኛውም የጨረታ አከፋፈት ተጫራቾች በአካል መገኘት ሳያስፈልግ የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም መከናወን አለበት፡፡

ለ) ለጨረታ አከፋፈት ዓላማ ማንኛውም ተጫራች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱየተሰጠውን የግል የሚስጥር ቁልፍ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ ወስጥ ለመንግስት መ/ቤቱ ማጋራት አለበት፡፡ የግል የሚስጥር ቁልፉንከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ለመ/ቤቱ ያላሳወቀተጫራች የመጫረቻ ሰነድ ሳይከፈት ከጨረታ ወጪ ይደረጋል፡፡

ሐ) የመንግስት መ/ቤቶች የግል የሚስጥር ቁልፍ በወቅቱ ያሳወቁ ተጫራቾችን የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ አከፋፈት ወቅት መክፈት አለባቸው፡፡

መ) የተጫራቾች የግል ሚስጥር ቁልፍ በወቅቱተልኮ በመ/ቤቱ ምክንያት የመጫረቻ ሰነዱ በጨረታ አከፋፈት ወቅት ካልተከፈተ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የመጫረቻ ሰነዱ በመ/ቤቱ የወስጥ አዲት እና ሲስተም አስተዳዳሪ ኃላፊ ወይም ባለሞያዎች ታዛቢነትበጨረታ ከፋች ቡድን እንዲከፈት ማድረግ አለበት፡፡

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ)የተደነገገው ቢኖርም የግል የሚስጥር ቁልፋቸወን ደህንነት የማጠበቅ ኃላፊነት የተጫራቾች ነው፡፡

ረ) የመንግስትመ/ቤቶች የጨረታወን አከፋፈት ሁኔታ እና ሂደት የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ ማያዝና ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ይፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 25 ኤሌክትሮኒክ ፐርቼዚንግ

1) የመንግስትመ/ቤቶች የዋጋ ማቅረቢያ፣የሚዕቀፍ ስምምነት ከገቡ አቅራቢዎች፣ ድንገተኛ፣ ወይም ጥቃቅን ግዥዎችን ለሚፈጸም ለዚህ ዓላማ በሥርዓቱ ላይ የተዘጋጀወን የፐርቼዚንግ ሥነ ሥርዓት ማጠቀም ይችላሉ፡፡
2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም ጥቃቅን ግዥ ማለት በግዥ ዕቅድ ወስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ከተቀማጠው የገንዘብ ማጠን ያልበለጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚፈጸም ግዥ ነው፡፡
3) በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ .፫ የተደነገገው ቢኖርምየመንግስት መ/ቤቶችበኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱየሚፈጸምየዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ወድድርንለሁሉም ተጫራቾች ክፍት ሊያደርጉይችላሉ፡፡
4) የዋጋ ማቅረቢያ ግዥን በተማለከተ በፌደራል የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ እንዲሁም የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ላይ የተቀማጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች የዋጋ ማቅረቢያ ግዥን እንደ አግባብነቱ ብሐራዊ ወይምዓለም አቀፍ ተደራሽነት እንዲኖረው በማድረግ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

## 26 የኤክትሮኒክ ሐራጅ

1) የመንግስትመ/ቤቶችኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በማጠቀም በጊዜ ወይም በዙር ላይ የተማሰረተ የግዥወይም የንብረት ሽያጭ ሐራጅ ሊያከናወኑ ይችላሉ፡፡
2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ አፈጻጸም የመንግስት መ/ቤቶች በተጫራቾች መካከል የሚኖርን ወድድር በሚይገድብ ሁኔታ የሃራጁን ዙር ገደብ ወይም ሀራጁ የሚቆይበትን ጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም ተጫራቾች በሌሎች ተጫራቾች ዋጋ ላይ ተማስርተው ለሚወገድ ንብረት ሽያጭ የወድድር ዋጋቸወን የሚጨምሩበትን ወይም ለግዥ አፈጻጸም የወድድር ዋጋቸወን የሚቀንሱበትን የገንዘብ ማጠን መቶኛበመወሰንከሃራጁ መጀመር አስቀድሞ በሥርዓቱ ላይ ለተጫራቾች ማሳወቅ አለባቸው፡፡
3) የጨረታ ማስከበሪያን በሚማለከት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው የተቀማጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በኤሌክትሮኒክ ግዥ የሐራጅ ጨረታ ላይ የሚሳተፍ ማንኛወም ተጫራቾች ከባንክ በሚሰጥ የጨረታ ማስከበሪያ ምትክ ኤጀንሲው ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀወን ቅጽ ተጠቅሞ የጨረታ ማስከበሪያ መተማመኛ ቅጽ በማቅረብ መወዳደር ይችላል፡፡
4) **የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታን በመጠቀም ግዥ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፤**

ሀ) የሚያሻማ ግልፅ ስፔሲፊኬሽን ያለው እና ለገበያ ተብሎ የተዘጋጀ ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ፣

ለ) በገበያ ላይ በቂ አቅራቢ ያለው ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ፣ እና

ሐ) ዋጋ ብቸኛ የማወዳደሪያ መስፈርት ለሆነበት የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ

ሲሆን ነው፡፡

5) የመንግስት መ/ቤቶች በዙር ለሚደረግ ሃራጅ በየዙሩ ማጠናቀቂያ፣ ወይም በጊዜ ገደብ በሚከናወን ሃራጅ ለወድድር የተሰጠው ጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሃራጅ ጨረታውጤቱን ወዲያውኑ ለተጫራቾች የሚያሳውቅ ስለመሆኑ ማከታተል አለባቸው፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዙር ላይ በተመሰረተ በሚደረግ ሃራጅወድድር ከመጀመሪያው ዙር ቀጥሎ ባለ ማንኛውም ዙር ላይማንም ተጫራች ዋጋ ካልሰጠ መ/ቤቶች አስቀድሞ በተደረገው ዙር ውጤት ማስረት የወድድሩን አሸናፊ ሊሚጡ ይችላሉ፡፡

## 27 የኤሌክትሮኒክ ግዥ ጨረታ ግምገማ

የጨረታ ግምገማን በተመለከተ በመንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ እንዲሁም በአፈጻጸም መመሪያዎቹ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከተው ሥርዓት ማስረት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ጨረታ ግምገማ ማከናወን አለባቸው፡፡

1) የግዥ ገምጋሚ ቡድን ግምገማውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ የተቀመጠውን የግዥ ግምገማ ስራ ፍሰት በመከተል ማከናወን አለበት፡፡

2) በጨረታው ከአንድ በላይ የሆኑ የገንዘብ ዓይነቶች የቀረቡ ከሆነ ለግምገማ ዓላማ ሁሉም የገንዘብ ዓይነቶችን ወደ ኢትዮጵያ ብር በመቀየር የዋጋ ወድድሩ መካሄድ አለበት፡፡

3) ለንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም ከአንድ በላይ የሆኑ የገንዘብ ዓይነቶችን ወደ ኢትዮጵያ ብር ለመቀየር ጥቅም ላይ የሚውለው የምንዛሬ ተመን የጨረታማቅረቢያ የሚጨረሻ ቀንን ጨምሮ ከጨረታ ማቅረቢያ የሚጨረሻ ቀን ወደ ኋላ ካሉት 28 ተከታታይ ቀናት መካከል ያለ ማንኛውም ቀን ተመን ሲሆን፣ ጥቅም ላይ የሚውለው የምንዛሬ ተመንቀንበጨረታ ሰነዱ ላይ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

4) የግምገማ ቡድኑ ከተጫራቾች መካከል በጨረታ ሰነዱ በቅድሚያ በተገለጸው የግምገማ ዘዴና መመዘኛ መስፈርት ማስረት በተደረገ ግምገማየተሻለ ሆኖ የተገኘውን ተጫራች በአሸናፊነት መምረጥ አለበት፡፡

5) **የግምገማ ቡድኑ በተቻለ መጠን ውሳኔዎችን በስምምነት ያስተላልፋል፤ ሆኖም በስምምነት ውሳኔ ማሳለፍ ካልተቻለ በድምጽ ብልጫ ይወስናል፤ ድምጽ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡**

## 28 የጨረታ ውጤትና አሸናፊ ተጫራችን ስለማሳወቅ፣

1) የመንግስት መ/ቤቶች የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም የግዥ ወይም ንብረት ሽያጭ ጨረታ ውጤት ለሁሉም ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ አድራሻዎቻቸው ማሳወቅ አለባቸው፡፡

2) በንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚገለጸው ውጤት የተሸነፉ ተጫራቾች የተሸነፉበትን ምክንያት እና በአሸናፊነት የተመረጠውን ተጫራች ጨምሮ እያንዳንዱ ተጫራች በውድድሩ ያገኘውን ደረጃ የሚገልጽና ተጫራቾች በውጤቱ ላይ ቅሬታ ካላቸው አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

3) በጨረታ ውጤቱ ላይ አቤቱታ ካልቀረበ ወይም አቤቱታ ቀርቦ በአዋጁና በመመሪያው የተደነገጉ የአቤቱታ ማጣራት ስነ ሥርዓትን ተከትሎ እልባት ካገኘ በኋላ የመንግስት መ/ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም ለአሸናፊው ተጫራች የአሸናፊነት ማስታወቂያ መስጠትና መረጃውንም ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

# ክፍል ሰባት

## አቤቱታ እና የጥፋተኝነት ሪፖርት ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ

### 29 የአቤቱታ ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1) በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ላይ የሚቀርብ ማንኛውምአቤቱታ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትሎ መቅረብ አለበት፡፡

2) **ጨረታ ከመከፈቱ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ይዘት ላይ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ከግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በሚሰጡ የማሻሻያ ወይም የማብራሪያ ምላሾች ላይ ቅሬታ ያለው ዕጩ ተወዳዳሪ የማሻሻያው ወይም የማብራሪያው ምላሽ ከደረሰው ወይም ምላሽ ሊሰጠው ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ በ**፭ (አምስት) **የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በቀጥታ ለቦርዱ ጽ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡**

3) የአቤቱታ አቅራቢዎችን የንግድ ተወዳዳሪነትእና የመንግስት መ/ቤቶችን መረጃ ሚስጢራዊነት የሚጎዳ እስካልሆነ ድረስ በመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ እና በቦርዱ የሚሰጥ ወሳኔ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

4) በአዋጁ አንቀጽ /፪ እና /፫/፣ እንዲሁም በመመሪያው አንቀጽ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋጋ ማቅረቢያና በሐራጅ በሚፈጸምግዥ ወይም ንብረት ሽያጭ ጨረታ ላይ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

### 30የጥፋተኝነት ሪፖርት ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1) ከመንግስት መ/ቤቶች ለኤጀንሲው የሚቀርብ ማንኛውምየጥፋተኝነት ሪፖርት እና ከኤጀንሲው የሚሰጥወሳኔየኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን መከተልአለበት፡፡

2) የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም በተከናወነ የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ጨረታ ጥፋት በመፈጸማቸው በጨረታ እንዳይሳተፉ የታገዱ ተጫራቾች እና አቅራቢዎች ዝርዝር በኤጀንሲው ድረ ገጽ ላይ እና በተጨማሪነት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱላይ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## የውል አስተዳደር

### 31 ውል ስለሚፈጸምና ስለሚስተዳደር

1) የመንግስት መ/ቤቶች የውል ሰነዱን ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ በማውረድ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር መፈራረም ያለባቸው ሲሆን ከፊርማው በኋላ የውሉን ሰነድ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መጫን ይኖርባቸዋል፡፡
2) የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው የውል ማስጀመር፣ የውል እቅድ ዝግጅት፣ የውል አፈጻጸም፣ የውል ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የውል ማጠናቀቅ እና የመሳሰሉ የውል አስተዳደር ተግባራትን ማከናወን አለባቸው፡፡
3) አፈጻጸሙ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ መምሪያ ላይ የሚገለጽ ሆኖ የመንግስትመ/ቤቱ መደበኛ፣ የማዕቀፍ ስምምነት፣ የግዥ ትዕዛዝ፣ የማዕቀፍ ስምምነት ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ዝርዝር ውል፣ የኮንሴሽን ወይም ሌሎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ከተዘረዘሩ የውል ስልቶች ወስጥ እንደ ግዥው ባህሪይ እና ዓይነት ተስማሚ የሆነውን በመምረጥ በሰነዱ ላይ መጥቀስ ይኖርባቸዋል፡፡
4) የመንግስት መ/ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱከተዘረዘሩ የጥቅል ዋጋ፣ የቁርጥ ዋጋ፣ የነጠላ ዋጋ እና በጊዜ ላይ የተመሰረተ የውል ዓይነቶች ወስጥእንደ ግዥው ባህርይና ዓይነት ተስማሚ የሆነውን በመምረጥ በውል ሰነዱ መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡
5) የመንግስት መ/ቤቶች ከአቅራቢዎች ጋር የገቡትን የውል አስተዳደር ሂደት የሚያሳዩ መረጃዎችን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው መያዝ አለባቸው፡፡
6) የንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ በሚጠይቀው መሰረት የአቅራቢዎችንየውል አፈጻጸም የሚያሳዩ መረጃዎቹን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ መያዝና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡
7) የመንግስት መ/ቤቶች በጨረታው አሸናፊ የተደረገው ተጫራች ውል ለመፈረም ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ መ/ቤቱ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በማገምገም ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች ጋር ውል ሊፈርም ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የሥነ ምግባር ድንጋጌዎችና እርምጃዎች

### 32 የመንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭኤሌክትሮኒክሥርዓት አጠቃቀም የሥነ ምግባር ድንጋጌዎችና እርምጃዎች

በአዋጁ እና በአፈጻጸም መመሪያዎቹ፣ እንዲሁም በመደበኛ የጨረታ ሰነዶች ላይየተደነገጉ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች እና እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን የሚጠቀም ማኛወም አካል ከዚህ በታች የተመለከቱትን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች ማክበር ይኖርበታል፡፡

1) ማንኛወም የሥርዓቱ ተጠቃሚ በሥራው አጋጣሚ ያገኛቸውን የተጠቃሚዎች የይለፍ ቃል፣ ሚስዕክቶች፣ ሰነዶች ወይም ሌሎች ኤሌክትሮኒክ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት የማጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡
2) የመንግስትመ/ቤት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በመ/ቤቱ ወስጥ ለተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር የሌሎች የሥርዓቱ ተጠቃሚዎችን መረጃ ማግኘትም ሆነ ለሌላ ሶስተኛ አካል መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
3) ማንኛወም የግል ይለፍ ቃሉ ያለፈቃድ ጥቅም ላይ ወሏል ወይም ሌሎች ያልተገቡ የደህንነት ጥሰቶች ተፈጽሚል ወይም ሊፈጸም ይችላል ብሎ የሚያምን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ተጠቃሚ ጉዳዩን ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡
4) ማንኛወም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ እና ይህን መመሪያ ተከትሎ በሚወጣው ዝርዝር የአጠቃቀም ማምሪያ የሚመለከቱ የደህንነት ማጠበቂያ እርምጃዎችን መከተል አለባቸው፣

5) አግባብነት ባለው የአገሪቱ ህግ መሰረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖየማንኛወም የኤሌክትሮኒክሥርዓቱ ተጠቃሚ መረጃ የተሳሳተ መሆኑ ከታወቀ ወይም ህገወጥ ወይም የተጭበረበረ ሆኖ ከተገኘ እንደሁኔታው መረጃው፣ ወይም ድርጊቱ በተጠቃሚው ግድልሽነት ወይም ታስቦበት የተፈጸመ ከሆነ የተጠቃሚው መለያ ከሲስተሙ ይሰረዛል፣

# ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33 የመንግስት ግዥን ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭን በመደበኛው አሰራር ስለመፈጸም

1) የመንግስት መ/ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የማጠቀም እና ተያያዥ ችግር ሲገጥማቸው ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ውጭ በመደበኛው አሰራር ግዥ መፈጸም የሚችሉትጥያቄያቸውን ለኤጀንሲው አቅርበው ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፡፡
2) የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሚያቀርቡት ጥያቄ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ግዥ ለመፈጸም ወይም ንብረት ለመሸጥ ያልቻሉበትን አሳማኝ ምክንያት እና ሰነዶች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

### 34 መመሪያወን ስለማሻሻል

ሚኒስትሩ ይህን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 35 የተጠቃሚዎች ማንዋል እና የአሰራር ሰነዶችን የማውጣት ሥልጣን

ኤጀንሲው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም መምሪያ፣ማንዋል፣ ቅጾችን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶች እና ሌሎች የአሰራር ሰነዶች ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

## 36 የተሻሩ መመሪያዎችና ህጎች

**ይህን የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ መመሪያ የሚቃረን በማንኛውም የፌደራል መንግስት መ/ቤት የወጣ ማንኛውም መመሪያ ወይም ማንዋል በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::**

## 37 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

***አዲስ አበባ ቀን*** ፪ሺህ ***ዓ.ም***

***አህመድ ሽዴ***